# ኖዚቤሌና ሦስቱ ጸጉሮች

Tessa Welch
Wiehan de Jager
Mezemir Girma
Amharic
Level 3

(imageless edition)

በድሮ ጊዜ ሦስት ሴቶች እንጬት ለመሰብሰብ ከቤታቸው ወጥተው ነበር።

ሞቃት ቀን ስለነበር ለመዋኘት ወደ ወንዝ ወረዱ።
ተጫወቱ፤ ውኃ ተራጩ፤ ዋኙ።

ድንገት ምሽት መሆኑን ተገነዘቡ። ወደ መንደራቸውም ተጣደፉ።

እቤታቸው ሊደርሱ ሲሉ ኖዚቤሌ እጇን አንገቷ ላይ አደረገች። የአንገት ጌጧን ረስታዋለች! ‹‹እባካችሁ አብራችሁኝ ተመለሱ!›› ብላ ባልንጀሮቿን ለመነቻቸው። ጓደኞቿ ግን በጣም እንደዘግየች ነገሯት።

ስለዚህ ኖዚቤሌ ወደ ወንዙ ብቻዋን ተመለሰች። የአንገት ጌጧንም አግኝታ ወደ ቤቷ ለመመለስ ተቻኮለች፤ ነገር ግን በጨለማ ውስጥ ጠፋች።

ከሩቅ ከአንዲት ጎጆ የሚወጣ ብርሃን አየች።
ወደሱም ሄዳ በሩን አንኳኳች።

ባልተጠበቀ ሁኔታ ዉሻ በሩን ከፈተላት። ‹‹ምን ፈልገሽ ነው?›› አላት። ‹‹ጠፍቻለሁ፤ እና ማደሪያ ቦታ ፈልጌ ነበር›› ብላ ነገረችው። ‹‹ነይ ግቢ፤ አለዚያ እነክስሻለሁ!›› አላት ዉሻው። ስለዚህ ኖዚቤሌ ገባች።

ከዚያም ዉሻው ‹‹ምግብ አብስዪልኝ!›› አላት። ‹‹እንዴ፣ እኔ እኮ ለዉሻ ምግብ ሰርቼ አላውቅም›› ብላ መለሰችለት። ‹‹ስሪልኝ፤ አለዚያ እነክስሻለሁ!›› አላት ዉሻው። ስለዚህ ኖዚቤሌ ለዉሻው ምግብ ሰራችለት።

ከዚያም ዉሻው <<አልጋዬን አንጥፊልኝ! አላት። ኖዚቤሌም <<እኔ እኮ ለዉሻ አልጋ አንጥፌ አላውቅም>> ብላ መለሰችለት። <<አንጥፊልኝ፤ ያለዚያ እነክስሻለሁ!>> አላት ዉሻው። ስለዚህ ኖዚቤሌ አነጠፈችለት።

በየቀኑ ለዉሻው ምግብ መስራት፣ ማጽዳትና ማጠብ ስራዋ ሆነ። ከዚያም አንድ ቀን ዉሻው ‹‹ኖዚቤሌ፣ ዛሬ ጓደኞቼን ልጠይቅ እሄዳለሁ። እኔ ከመምጣቴ በፊት ቤቱን አጽጂ፤ ምግብ ስሪ፤ የሚተጣጠቡትንም ነገሮች እጠቢ›› አላት።

ዉሻው እንደሄደ ኖዚቤሌ ከራሷ ላይ ሦስት ጸጉሮችን ከጭንቅላቷ ላይ ነቀለች። አንዱን ጸጉር ከአልጋው ስር፣ አንዱን ከበሩ ኋላ፣ እና ሌላውን ደግሞ በከብቶቹ በረት አስቀመጠቻቸው።

ዉሻዉም እንደተመለሰ ኖዚቤሌን ፈለጋት። ‹‹ኖዚቤሌ፣ የት ነሽ?›› ብሎ ተጣራ። ‹‹አልጋው ስር ነኝ›› አለ የመጀመሪያው ጸጉር። ‹‹በሩ ጀርባ ነኝ›› አለ ሁለተኛው ጸጉር። ‹‹በረት ውስጥ ነኝ፣›› አለ ሌላኛው ጸጉር።

ከዚያም ዉሻው ኖዚቤሌ እንዳታለለችው ገባው። ስለዚህ ወደ መንደሩ እየተሯተሯጠ ፈለጋት። የኖዚቤሌ ወንድሞች ግን ትላልቅ ዱላዎች ይዘው እየጠበቁት ነበር። ውሻው ተመልሶ ሮጠ፤ ከዚያም በኋላ በመንደሩ በጭራሽ ታይቶ አያውቅም።

# Storybooks Canada

storybookscanada.ca

## ኖዚቤሌና ሦስቱ ጸጉሮች

Written by: Tessa Welch
Illustrated by: Wiehan de Jager
Translated by: Mezemir Girma

This story originates from the African Storybook (africanstorybook.org) and is brought to you by Storybooks Canada in an effort to provide children's stories in Canada's many languages.

This work is licensed under a Creative Commons Attribution 3.0 International License.